# በአውራምባ ታይምስ የተቆረጠው የታማኝ ቃለ-መጠይቅ

*አርቲስት ታማኝ በየነ ከአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ጋር የቃለ-ምልልስ እንዲያደርግ ከአዘጋጁየ ቀረበለትን ጥያቄ ተቀብሎ ቃለ-ምልልስ አድርጎ ነበር፡፡ ቃለ-ምልልሱ በጋዜጣው ታትሞ ከወጣ በኋላ ግን: ለጋዜጣው አዘጋጅ በላከው ደብዳቤ "ቃለ ምልልሱን አነበብኩት፡፡ ስሜንና ፎቶግረፌን ከመያዙ በቀር የኔ ሀሳብ የምለው አንድም በውስጡ ባለመኖሩ በጣም አዝኛለሁ፡፡" ሲል ቅሬታውን ገልጿል፡፡ የአውራምባ ታይምስ አዘጋጅ ቃለ-ምልልሱን እንዳለ ቢያወጣው በህይወቱ ላይ አደጋ ሊያስከትልበት እንደሚችል ገልጾ ሙሉውን ባለማተሙ ይቅርታ ጠይቋል፡፡ ለአንባቢያን ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ሙሉውን ቃለ-ምልልስ እንደሚከተለው አውጥተነዋል፡፡*

***ከአውራምባ ታይምስ፡-*** *እንግዲህ በአሁኑ ሰዓት ለአገር ለወገን ትልቅ ስራ ሰርተው ያለፉ ታላላቅ ኢትዮጵያወገኖችን በማስታወስ ብዙ እንቅስቃሴዎችን በማከናወን ላይ እንደምትገኝ ይታወቃል፡፡ እስኪ ለአገር ውስጥ አንባቢ ጠቅለል አድርገህ ብትገልጽልኝ?*

*ታማኝ:-* እንደ ትውልድ ብዙ እዳ አለብኝ ብየ አስባለሁ ስለዚህ ከእዚህ በፊት በተለያየ ሙያ ሀገራቸውን ያገለገሉ ኢትዮጵያዊያንን ከተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር በመሆን እውቅና ዕንሰጣለን እናመሰግናቸዋለን በዚህ መሰረት የኪነጥበቡን ሙያ ብንወስድ ትናንት ጋብቻ ከልክል የነበረ ሙያ ነው በዚያ ዘመን የነበሩ ሙያተኞች ተዋርደው ተንቀው ግን ጥርሳቸውን ነክሰው ፀንተው ታግለው በከፈሉት ህይወት ነው የዛሬው ትውልድ ባለሙያዎች በመላው አለም እየተዘዋወሩ ስራቸውን ሲያቀርቡ ሽህ ህዝብ ተሰልፎ የሚያያቸው ስለዚህ ባለችን አቅምና ትርፍ ጊዜ ይህን ውለታ ለዋሉልን እንደነ ጋሽ ፀጋየ ገ/መድህን ታላቁ ጥላሁን ገሠሠ ጋሽ ተስፋየ ለማ አለባቸው ተካ ለሌሎቹም ምስጋና አቅርበናል እውቅና ሰተናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መቸም በዓለም ላይ መለኪያ የሌለው ስጦታ ህይወት ነው ሀገራችን ፈተና ውስጥ ስትወድቅ መተኪያ የሌላትን ህይወታቸውን ለመስጠት በግምባር የዘመቱ የኢትዮጵያ ወታደሮች የደርግ ወታደር ተብለው ተበትነው ለማኝ እንዲሆኑ ተደርጓልይሄን እዚሁ ላይ ልተወው ምክኒያቱም በዚህ ዙሪያ የተቋቋመው ኮሚቴ ከፖለቲካ ነፃ ስለሆነ የእኔ የግል ሃሳብ የኮሚቴውም ተደርጎ እንዳይወሰድ ስለምፈራ ነው፡፡ ለማንኛውም በ1969 ሶማሊያ ሀገራችንን በወረረችበት ወቅት የኢትዮጵያ አየር ሃይል ያስመዘገበው ድል በታሪክ የተመዘገበ ነው ከያኔወቹ ጀግኖች አንዱ ብ/ጄኔራል ለገሰ ተፈራ ነው ይህ ጀግና 5 የሶማሊያን አውሮፕላን የጣለና በሶማሊያ ሜካናይዝድ ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶ በመጨረሻ አውሮፕላኑ ተመታ ስትወድቅ በጠላት እጅ ወድቆ ለ11 አመት ከመሬት በታች ጨለማ ውስጥ ታስሮ ከቆየ በኋላ በአለማቀፍ ቀይ መስቀልና በወቅቱ በነበረው የኢትዮጵያ መንግስት እርዳታ ከእስር ተፈቶ በወቅቱ የሀገሩቱን የመጨረሻ ነው የተባለውን ሜዳሊያ ተሸልሟል ፡ታዲያ ይህንን ጀግና ነው በስደት እንዳልባሌ እቃ ተጥሎ ያገኘነው ይህ የእኛ ኮሚቴ የጀግና ምሽት አዘጋጅቶ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት የክብር ሽልማት ሸልሞ ለሀገራችን ላደረከው በሙሉ እናመሰግንሀለን ብሎታል በዘንድሮው አመት ደግሞ ሌሎች ጀግኖችን አፈላልገን ማለትም በሸህ1969 ዓም ናቅፋ ላይ በሻቢያ ተከቦ የሚገኘውን የ15ኛ ሻለቃ ጦርን ለማስለቀቅ የአየር ወለድን ጦር ይዘው ካለማቀፍ ህግ ውጭ ከ2000 ጫማ ከፍታ ላይ በመዝለል ከ15ኛ ሻለቃ ጋር በመገናኘት ለስድስት ወር ከተዋጉ በኋላ የሻቢያን ከበባ በመስበር ከወገን ጦር ጋር ለመቀላቀል በመብቃታቸው በወቅቱ የሃገሪቱን የመጨረሻ የተባለውን ሜዳሊያ ለመሸለም የበቁትን ብ/ጄኔራል ተስፋየ ኃ/ማርያምን እንዲሁም ገና ትምህርታቸውን ከአሜሪካን ሀገር ጨርሰው እንደተመለሱ ወደ ምስራቅ ኢትዮጵያ ዘመቱ ከዚያም በድል ወደ ኤርትራ አቀኑ እስከ 1981 ድረስ ያልተሳተፉበት የውጊያ ግንባር የለም ለሀገራቸው ላደረጉትም ውለታ በጊዜው የሁለተኛ ደረጃ የላቀ የጦር ሜዳ ሜዳሊያ የተሸለሙትን ብ/ጄኔራል ካሳየ ጨመዳን እንዲሁም በሶማሊያ ውጊያ በሚሊሻነት ዘምቶ አንድ ታጣፊ ክላሽንና ቦምብ ይዞ ገብቶ ሶስት ታንኮችን ያቃጠለ ሁለት የሶማሊያ አዋጊ መኮንኖችን የደመሰሰ በዚሁ ጀግንነቱ የጀግና ሜዳሊያ የተሸለመውንና በአኑ ስዓት በአዲስ አበባ በኩሊነት የሚተዳደረውን ሚሊሻ አሊ በርኬን መርጠን ሁለቱ ጄኔራሎች እዚሁ አሜሪካ ድረስ መተው ሽልማታቸውን ተቀብለዋል ሚሊሻ አሊ በርኬ ግን አድራሻው በጊዜው ባለመገኘቱ ሊመጣ አልቻለም ነበር ዝግጅቱ ከተኪያሄደ በኋላ ግን አቶ ቅዱስ ሀብት በላቸው የተባሉ ኢትዮጵያዊ ከአውስትራሊያ አድራሻውን ስላገኙልን ሽልማቱን ኢትዮጵያ ድረስ ልከንለት ተረክቧል፡፡ የጄኔራል ደምሴ ቡልቶን በተመለከተ ደግሞ ልጃቸው የአባቱን ታሪክ በመፅሀፍ ሲያቀርብ ታሪኩ ልቤን ስለነካው በመፅሀፉ ምረቃ እለት የጄኔራሉን አጭር የህይወት ታሪክ በፊልም አቀናብሬ አቅርቢያለሁ፡፡እንዲህ እንዲህ እያልኩ ድርሻየን ለመወጣት እሞክራለሁ፡፡

***ከአውራምባ ታይምስ:-*** *ብዙ ኢትዮጵያዊያን ለህግ የበላይነት፣ለሰብአዊ መብት መከበርና ለዴሞክራሲ መስፈን እየታገሉ፤የተለያየ ጥያቄ ሲቀርባላቸው ደግሞ ፖለቲከኛ አይደለሁም ሲሉ ይደመጣሉ? በአንተ እምነት አንድ ሰው ፖለቲከኛ የሚያሰኘው ምንድነው? ፖለቲከኛ ነኝ ብለህስ ታስባለህ?*

***ታማኝ:-*** ጥልቅና ከባድ ጥያቄ ነው ፡፡ስለፖለቲከኛነት እኔ እንደሚመስለኝ ከምናገር በዚህ ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ሰዎች ቢናገሩ ደስ ይለኝ ነበር፡፡የሚሰማኝን ለመግለፅ ያህል በኢትዮጵያ ውስጥ ፖለቲከኛ መሆን ዘጠና በመቶ አደጋ አለው ብየ አምናለሁ፡፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን እንኳን ብንመለከት አፄ ኃ/ሥላሴ ወደ ስልጣን ሲመጡ ተቀናቃኛቸው የነበሩት ልጅ እያሱ እንኳን የት እንደ ደረሱ እስከ ዛሬ ድረስ አናውቅም፡ስለዚህ ወደ ፖለቲካ ስትመጣ ወይ ስልጣን ትይዛለህ ያለበለዚያ ትጠፋለህ፡፡መለስ ብለን አበበ አረጋይን እንመልከት ፋሽሽት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በተቆጣተረበት ጊዜ በአዲስ አበባ ዙሪያ አፍንጫው ስር ሆነው አምስት ዓመት የታገሉ አርበኛ ናቸው በ1953 በተደረገው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ቤተመንግስት ውስጥ የተረሸኑት፡፡

ሌላውን ታላቅ ኢትዮጵያዊ አክሊሉ ኃብተወልድን ብንወስድ በዲፕሎማሲ ትግል ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ እንድትመለስ ያደረጉ ከልጅነታቸው ጀምሮ ሀገራቸውን በቅንነት ያገለገሉ ኢትዮጵያዊ የአስር ደቂቃ የኑዛዜ እድል እንኳ ሳይሰጣቸው ነው የተረሸኑት፡፡

***ከአውራምባ ታይምስ:-*** *የደርግና ኢህአዴግንም አያይዘህ ብትገልፅልኝ*

***ታማኝ:-*** ደርግማ ከአርበኝነት ጀመሮ እስከ ዲፕሎማሲ ዘመናዊት ኢትዮጵያ እንድትፈጠር እድሚያቸውን ሙሉ ያገለገሉ 60 ኢትዮጵያዊያንን በመረሸን ስልጣኑን ጀምሮ በአራቱም ማዕዘን ሀገራቸውን ከጠላት ሲከላከሉ የኖሩትን ከፍተኛ የጦር መኮንኖች በመረሸን ነው የስልጣን ዘመኑን ያጠናቀቀው የኢህአዴግ ግን በዘዴው ለየት ይላል እንደነ ሙሉዓም (የአዲስ አበበ ከንቲባ የነበረው) በድንገተኛ አደጋ ሞተ ትባላለህ ወይም የቁም ሞት ትሞታለህ፡፡ ለምሳሌ አቶ ታምራት ላይኔን ብትወስድ 17 ዓመት አብረው ታግለው መጡ በተከበሩበት ፓርላማ ውስጥ ወስደው ብመከር ብመከር አልሰማ ብየ ነው አስብለው ለቀቋቸው ከልጅነታቸው ጀምረው አብረዋቸው የታገሉትን አቶ ሰየ አብርሃን መላ ቤተሰባቸውን ሰብስበው አሰሯቸው እንግዲህ እነዚህንና ሌሎችንም ያየ ትውልድ ፖለቲካን ቢፈራ አትፈርድም፡፡ ነፃ እርምጃ ቀይ ሽብር የሚሉት ቃላቶች በራሳቸው እንዴት ያስፈራሉ መሰለህ ከዚህ በመነሳት ፖለቲከኛ ከመባል የሚመጣውን ውጤት በመፍራት ይመስለኛል እኔ ፖለቲከኛ አይደለሁም የምንለው፡፡ ለእኔ ፖለቲካ ማለት በጋራ በምንኖርበት ሀገር ውስጥ እኩል እንድንሆን የምናሰፋውን ልብስ ዲዛይን የምናደርግበት ነው፡፡ አሁንም እኔን ብትጠይቀኝ ፖለቲከኛ አይደለሁም ነው የምልህ በፖለቲካ ውድድር ገብቼ ስልጣን ለመያዝ ፍላጎት ስለሌለኝና ከፖለቲካው ይልቅ ኪነጥበብን የበለጠ ስለምወድ ነው፡፡ በፈራን ቁጥር ግን ነፃነታችንን እያጣን ነው የምንሄደው ስለዚህ የግድያን አዙሪት ለማቆም የፍህርሀትን ቀንበር ለመስበር አንድ ጌዜ አምርረን እንታገል ከፖለቲካ አንሽሽ፡፡

***ከአውራምባ ታይምስ:-*** ከአንድ አመት በፊት በሰጠኸኝ ቃለምልልስ "በስልጣን ላይ ያለው አካል ወደ ልቦናው እንዲመለስ ዝቅ ብዬ እመክራለሁ" ብለህ ነበር፡፡ ምክርህ ተቀባይነት አግኝቷል?

***ታማኝ:-*** እኔ እንደ አንድ ዜጋ ቅን ነው ብየ ያሰብኩትን አቅርቤለሁ፡፡ ከእኔ በተሻለ ደግሞ የፖለቲካ ድርጅቶች ላለፉት 18 ዓመታት ብሄራዊ እርቅ ፡ጥምር መንግስት፡ የሽግግር መንግስት ሌላም ሌላም ተብሏል::ከመንግስት በኩል ግን አንድም ይሄን ጉዳይ በቅንነት ማየት የፈለገ የለም ፡፡እኔ የማዝነው ግን ከትናንት ይቅር ከዛሬ እንኳን ለመማር ለምን እንደማይፈልጉ ነው;ምን አይነት የተረገመ ወንበር ነው
ኮሎኔል መንግስቱ እንኳን ይሄን ጦርነት በጦርነት ብቻ ማሸነፍ ያስቸግራል ድርድር ይሞከር ብለው የጦር አዛዦቻቸው ሲያማክሩዋቸው ሀገሪቱዋን ለወንበዴ ልትሸጡ ነው ብለው ሁሉንም ረሽነው በመጨረሻ ሀገሪቷን ለእነዚሁ ወንበዴ ላሉዋቸው አስረክበው ሄዱ፡፡ ብሄራዊ እርቅ እኮ ቀላል ነገር አይደለም ለልጆቻችን የሰከነና የተረጋጋ ሀገር መስጠት ማለት ነው፡፡መቸም እነ አቶ መለስ ከህውሃት ከኢህአዴግም በላይ ልጆቻቸውን የሚወዱ ይመስለኛል፡፡በእርግጥ ልጆች በአባቶቻቸው ሀጢያት ተጠያቂ አይደሉም ፡፡ አንዳንድ የቀድሞ የደርግ ባለስልጣን ልጆች ሰው እንዳያውቃቸው ሲሳቀቁ አይቻለሁ፡፡የእነሱ ልጆች ላለመባል ሲደበቁ ነበር፡፡አንድ ምሳሌ ላንሳ የአቶ አሰፋ ማሩ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበርና የኢሰመጉ አባል የነበረ በጠራራ ፅሀይ አዲስ አበባ ላይ ተረሽኗል ታዲያ የአሰፋ ልጆች ስለ አቶ መለስ ልጆች ምን ስሜት ይኖራቸዋል

የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ልጅ ስንት አመት ሙሉ ስታለቅስ ስታድግ ስለ አቶ መለስ ልጅ ምን አይነት ስሜት ይኖራታል የጋዜጠኛ የሰርካለምና የጋዜጠኛ እስክንድር ልጅ ስታድግ የት ተወለድሽ ሲሉዋት እድሜ ለነ አቶ መለስ እስር ቤት ነው የተወለድኩት ትላለች፡፡እንዴት በ18 አመት ውስጥ መስከን ያቅታል፡አሁንም እልህ ንዴት ፡እንደ ገና ከሰሙኝ ስለ ልጆቻችሁ ስትሉ ስከኑ ስከኑ ስከኑ እላለሁ

***ከአውራምባ ታይምስ***- ምርጫ 97 ተከትሎ በእስር የተዳረጉ ወገኖችን ስላሸማገሉት ወገኖች ያለህ አስተያት ምንድን ነው?

***ታማኝ***:- በእውነቱ መሰረታዊ የሆነ ጥያቄ ነው ያነሳህው ፡፡እንዲያውም ለዚህ ሁሉ መከራችን አንዱ ምክኒያት ይሄው ይመስለኛል፡፡በኢትዮጵ ውስጥ ሽማግሌዎች ትልቅ ቦታ ነበራቸው፡፡ሽማግሌ የመስማት እሴት ነበረን፡አሁን እኮ በሞራል ሁሉ ሞተናል፡፡የሃይማኖት አባቶች ይህን አለም የናቁ በክርስትና እምነት ደግሞ ሞትም ህይዎትም እየሱስ ብቻ ነው ብለው የሚያምኑ ነበሩ፡አሁን እኮ በሀገር ላይ ይሄ ሁሉ ግፍ ሲፈፀም እያዩ ምንም እንዳልተደረገ የሚሰብኩ እንዲያውም ጳጳሶቹ ተጣልተው ፖለቲከኞቹ የሚያስታርቋቸው ጊዜ ላይ ደረስን ፡፡የምርጫ 97 ግድያ እንዲያጣራ ከተመረጡት የሃይማኖት አባቶች አንዱ የሙስሊሙ ተወካይ እኮ መንግስት የወሰደው እርምጃ ተገቢ ነው ብለው ነው ድምፅ የሰጡት፡፡ ክርስቲያን ስትሆን ስጋህን ንቀህ ለዚያኛው አለም ማሰብ ሲገባህ ጥይት በማይበሳው መኪና የሚሄዱ በወርቅ ጫማ የሚዋቡ አባት አገኘን፡፡ በየአለሙ ስንዴ እየለመን እየበላን ባለ ወርቅ ጫማ አባት አሉን ስንል አናፍርም ከዚህ በላይ መሞት አለ፡፡

በምርጫ 97 የታሰሩትን የቅንጅት አመራሮችንና ጋዜጠኞችን ለማስፈታት በሽምግልና ተሳተፍን ያሉትን ሰዎች እዚህ ዋሥግጸን መተው ፕሮፌሰር ኤፍሬምንና ፓስተር ዳንኤልን ቁጭ ብየ አነጋግሪያቸዋለሁ፡፡እኔ የአይንም የጆሮም ምስክር ነኝ፡፡ በወቅቱ እንዴት አልቅሰውና ተንበርክከው የቅንጅት መሪዎችን እንደለመኑ እያለቀሱ የነገሩኝ ሰዎች ዛሬ ብርቱካን በግፍ ታስራ አንድ አመት ሲሞላት እንኳ ወተው እውነቱን እንኳን ለመናገር አለመቻላቸው፡ የኢትዮጵያ ጀግና ብየ በህዝብ ፊት እግሩን የሳምኩት ሀይሌ ገ/ስላሴም ዝም ሲል በሀይማኖትም በሞራልም የደረሰብንን ኪሳራ ያሳያል፡፡ይሄ ትውልድ እንዴት አንድ የሚያምነውና የሚከተለው አርአያ ሰው ያጣል በጣም አዝናለሁ፡፡

***ከአውራምባ ታይምስ***- አህአዴግን ግለጸው ብትባል ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በስንት ምዕራፍ ከፋፍለህ ትገልጸዋለህ?

***ታማኝ***:- ኢህአዴግ የተለያየ ማሊያ ይለብሳል እንጅ የሚጫወተው ያው ለአንድ ቡድን ነው፡፡ እኔ ምን ያህል እንደሚፈቀድላችሁና ምን ያህሉን እንደምታወጡት አላውቅም፡፡ የ1983 ኢህአዴግ በጣም የተለየ ነው፡፡ በሦስት እንኳን ከፍለን እንይው ብንል:

ከ1983-ኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ያለው ኢህአዴግ
በፀረ ኢትዮጵያዊነት የሰከረ ኢህአዴግ ነበር
የኢትዮጵያ የሆነውን ሁሉ ጠልቶ፡

- ለ50 አመት የተገነባውን የኢትዮጵያን የመከላከያ ሀይል አፈረሰ
- ኢትዮጵያ በህጋዊ መንገድ የምታገኘውን ወደቧን አስረክቦ ከባህር አገለላት
- እነ አቶ ኢሳያስን ያስደስታል ያለውን ሁሉ አደረገ፡፡ ኤርትራ በአፍሪካ ትልቋ ቡና ላኪ ሀገር እስክትባል ድረስ እነ አቶ ኢሳያስ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳሻቸው ሆኑ፡፡ ይባስ ብለው አዲስ አበባ ውስጥ የራሳቸው እስር ቤት ከፍተው የፈለጉትን እስከማሰር ድረስ ፈቀደ፡፡
- ያለፉት የኢትዮጵያ መንግስታት ለብሄራዊ ደህንነት ሲሉ ያደረጉትን ብርቱ ሚስጥር ሳይቀር በማውጣት ለሶማሊያ መፍረስ ተጣያቂ ኢትዮጵያ ናት ብለው ዶክመንቱን በመፅሄት ሳይቀር አትሞ አወጣ፡፡

ከኤርትራ ጋር ያለን ፍችም ቢሆን በአግባቡ ይሁን ያሉትን ፕሮፌሰር አስራትን እንዳይፈቱ አድርጎ አሰራቸው፡፡

በኤርትራ ውጊያ የተሳተፉ የአየር ሃይል አባሎች እየተለቀሙ ታሰሩ አራት የአማራ ሽማግሌዎች ተመርጠው የአማራው መንግስት ላደረሰው በደል ሻቢያን ይቅርታ እንዲጠይቁ በኢህዴን ተመርጠው ወደ አስመራ ተልከው በአቶ ኢሳያስ እግር ስር እንዲወድቁ አደረገ፡፡

የክሱም ሀውልት ለወላይታው ምኑ ነው ያሉትን ጠ/ሚንስትር መለስን ተከትለው የ ኦህዴድ አቶ ሱሌማን ደደፎ ለእኔ ያልሆነች ኢትዮጵያ ሽህ ቦታ ትበጣተስ ሲሉ የእህዴን አቶ ዳዊት ዮኃንስ ደግሞ ኢትዮጵያ በታሪኳ ጦርነት አሸንፋ አታውቅም አሉ፡፡

በዚህ መልክ ነው የ1983ቱ ኢህአዴግ በኢትዮጵያዊነት ላይ የዘመተው ከዚያ በኋላ ያለው ኢህአዴግ ደግሞ የኤርትራ ጦርነት ሲነሳ ተቀየረ ብለን ነበር፡፡በነገራችን ላይ ኢህአዴግ ከኢትዮፕያ ህዝብ ጋር ሊታረቅበትና አገሪቷን ወደ ተሸለ ቅጣጫ የሚወስድበት ትልቅ እድል ገጥሞት ነበር ነገር ግን በእልህ በንዴትና ትዕቢት እድሉን የሚያበላሽድርጅት ነው፡፡ ያን ያህል ኢትዮጵያዊ ባድመ ድረስ ሄዶ የወደቀለት ጉዳይ በምን መልኩ እንደ ተጠናቀቀ እኛም ታሪክም መዝግበናል፡፡አሁን ወ/ት ብርቱካንን ይቅርታ ጠይቃ አልጠየኩም ብላለችና ቃሏን ቀየረች ብለው እድሜ ልክ ብለው ሲያስሯት ይገርመኛል ምክኒያቱም ያኔ ባድሜ ለእኛ ተወስኗልና ውጡና ጨፍሩ ያሉት አቶ ስዩም መስፍን በዚህ አይነት ስንት አመት ሊፈረድባቸው ነው; አቶ መለስም በ1983 ዓ/ም የሽግግር መንግስት ሲቋቋም በጉባኤው መዝጊያ ላይ ያሉትን ልጥቀስ ከአሁን በኋላ የኢትዮጵያ ወጣት የሚረግፍበት የኤርትራ ጦርነት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዘግተነዋል የኢትዮጵያና የኤርትራ እናቶች ሀዘናችሁን እየተካፈልን በሌላ በኩል ግን ብስራት ነጋሪ ሆነናል ከእንግዲህ ጦርነት አይኖርም ነበር ያሉት ፡፡ከዚህ አዋጅ በኋላ ባድሜ ላይ ያ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ተሰዋ፡ታዲያ አቶ መለስ ባላከበሩት ቃላቸው ስንት አመት ይፈረድባቸው፡፡

ሦስተኛው ደግሞ ከ1997 በኋላ ያለው ኢህአዴግ ነው:

ከ1997 በኋላ ያለው ኢህአዴግ የቆሰለ አውሬ ነው ድንጉጥ ተጠራታሪና ፈሪ ነው የጉዳዩ ባለቤትና የአይን ምስክር የሆነው የ ኢትዮጵያ ህዝብ እያለ እኔ ከዚህ እንደዚህ ሆነ እንደዚያ አልልም ግን አንዳንዶቹን ለማስታወስ የሚችለውን ገደለ እስርቤት ጠቦ የጦር ካምፖች እስርቤት እስኪሆኑ ድረስ ወጣቱን በሙሉ አሰረ የህዝቡ ብቸኛ መተንፈሻ የነበሩትን ጋዜጠኞች በሙሉ አሰረ ያመለጡ ተሰደዱ በመላው አለም ያሉትን ያሙኛል አይወዱኝም ያላቸውን በሙሉ በዘር ማጥፋትና በሀገር ክህደት ከሰሰ

-ትልልቆቹን ፖለቲከኞች እያስፈረመ የኔ ቢጤውን ደግሞ ቪድዮና ፎቶ እያነሳ ዋ ሁለተኛ እያለ ፈታቸው የሰራዊቱን የደህንነቱንና የፖሊስ ቁልፍ ቦታወችን በሚያምናቸው ሰዎች አጠናከረ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም መግደል ብቻውን እንደማያዋጣ ሲያውቅ ከጠመንጃ ቀጥሎ ፍርድቤት ነው ብሎ ወሰነ

ልክ ንፁሃንን ተኩሰው እንደሚገድሉ ወታደሮች ንፁሃንን በህግ መሳይ ጥይት ለመግደል የሚችሉ የህግ ሙያ የተማሩ ሰዎችን አሰማርተው አዲስ ግድያ ጀመሩ የሚያሳዝነው እነዚህ በህግ ስም የሞት ፍርድ የሚያረቁ የሚፈርዱ አቃቢ ህግ ነን ብለው የሚቆሙ እንዴት እንደሚተኙና ለልጆቻቸው የሚተውትን የስም እዳ እንዴት እንደማያስቡ ይገርመኛል ፡፡ በተለይ የአማራ ክልል የኦሮሞ ክልል የደቡብ ክልል የሌላም ክልል ፕሬዝዳንቶች እየተባሉ የተቀመጡ ሰወች የአቶ መለስ የፖለቲካ ዝናብና ፀሀይ መከላከያ ጃንጥላ እንጅ መለስን የሚከራከሩ አይደሉም ስለዚህ የሀገሪቱ እጣ ባንድ ሰው እጅ ወድቋል ኢህአዴግም ጥሩ መንገድ እየሄደ አይደለም ታሪክ ደግሞ ይህንንም እየመዘገበ ነው፡፡

***ከአውራምባ ታይምስ፡- መገለጽ አለባቸው የምትላቸው ተጨማሪ ነገሮች ካሉ እድሉን ሰጥቼሃለሁ***

ብዙዎቹን የዳሰስናቸው ይመስለኛል፡ ለማጠቃለያ ግን እንደሚወራው ማለትም እንደ አስፋልቱ መስፋት እንደ ህንፃው መገንባት እንደ ኢኮኖሚው ማደግ አይመስለኝም ያለብን ችግር፡፡ ያለብን ችግር ከዚያ በላይ ነው ብየ አስባለሁ፡፡ ስለሆነም ችግሩን አውቀን የምንነጋገርበት መድረክ ፈጥረን አሁኑኑ እልባት ካላበጀንለት እየኖርን ያለነው በህመም ማስታገሻ ይመስለኛል፡ካንሰር ሊሆን የሚችል በውስጣችን እያለ ማስታገሻ እየወሰድን መኖር በሽታውን እያባበልን ለትልቅ ውድቀት የምንዳረግበት ችግር ያለ ይመስለኛል፡፡ ይሄ የብሄር ብሄረሰቦች መብት ተብሎ የሚነገረን ነገር በእውነታው የሌለ ስለሆነ ለበለጠ መራራቅና ላዩነት እየዳረገን ነው ስለዚህ በጉዳዩ ላይ በግልፅ ብንነጋገር ደስ ይለኛል፡፡ ወደ ኋላ ተመልሸ በሽግግር መንግስቱ የሰኔ ጉባኤ ላይ የአቶ መለስን ንግግር ልጥቀስ አምባ ገነኖች በሰላም እምቢ ያሉንን መብታችንን በሀይል አንበርክከናቸው ዲሞክራሲን ከዋናዋ ባለቤቶች ጋር እንዴት እንዳገናኘናት እኛም እነሱም በህይወት እያለን

አሳይተናቸዋል፡፡ ነበር ያሉት ታዲያ ዛሬ መብታችንን ተገፏል ያሉ ኢትዮጵያዊያን ለመብታቸው ሲታገሉ ሽብርተኛ የሚባሉት በምን ሂሳብ ነው፡፡ በቅርቡ ራሱ መንግስት ባወጣው መግለጫ በሰራዊቱ ውስጥ የነበሩ ጄኔራሎች የመንግስት ግልበጣ ለማድረግ ሞክረው ተያዙ ብሎናል ፡፡ዲመፐክራሲ ባለበት ሀገር ግልበጣን ምን አመጣው ችግር አለ ማለት ነው፡፡በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ ጉባኤ ላይ የአሜሪካው ዲፐሎማት ሲናገሩ በኢትዮጵያ ያለው ከፍተኛ የመንግስት ስልጣኖች በአንድ ብሄረሰብ የተያዙ ናቸው ብለዋል ይሄ ጥሩ ምልክት አይደለም ፡፡አሁን መንግስት ለመገልበጥ ተብለው ከተያዙትና እድሜ ልክ የተፈረደባቸው የሰራዊቱ አባላት የነበሩት የአንድ ብሄረሰብ አባላት ናቸው፡፡እንዴት የአንድ ብሄረሰብ አባላት አንድ አይነት ሀሳብ ያስባሉ ችግር አለ ማለት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ በሌሎች የብሄረሰቡ አባሎች ልብ ውስጥ ጥሩ ስሜት አይፈጥርም፡ኦነግ እየተባሉ የሚታሰሩ የኦሮሞ ልጆች ጉዳይ በሌሎች ኦሮሞዎች ልብ ውስጥ ጥሩ ነገር ይፈጥራልን፡በሌላው በሌላውም ወገን እየተካሄደ ያለውስ በጋምቤላው በኦጋዴኑ የተካሄደውስ አብሮ የሚያኗኑረን ነውን በጅማ የታየው የሀይማኖት ግጭት ችግሩን ከመሰረቱ ነቅለነዋል ወይስ የህመም ማስታገሻ ወስደን አልፈነዋል፡፡የደበቅናቸውና ያፈናቸው ትላልቅ ችግሮች በውስጣችን አሉ ሰብረን ወጥተን ካልተነጋገርን እንጠፋለን፡፡ በዘር ጉዳይ የሚነሳ ነገር ከመተላለቅ በስተቀር አሸናፊ አይኖረውም፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲነጋገር እለምናለሁ፡፡ለዚህ ሁሉ ችግር መፍትሄው ደግሞ አንድ ብቻ ነው ስለዚህ ኢትዮጵያ እኩል የሁላችን እንድትሆን ሁላችንም ወደ ትግሉ እንቀላቀል፡፡ነፃነታችንን ከራሳችን በቀር ማንም አይሰጠንም፡፡